በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን

መዝሙርና ሥነ ጥበባት ክፍል

፳፻፲፩ ዓ.ም

የሠርግ መዝሙራት

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ

፮. ሙሽራዬ

ሙሽራዬ/፫/ አበባዬ

ከጎንህ የምትሆን እህት አገኘህ
የእኛማ ሙሽራ እንኳን ደስ አለህ
የእግዚአብሔር ፈቃዱ ለዚህ ካበቃችሁ
ቤታችሁ ይመረቅ በፍቅር ያጽናችሁ
ወንድም አግኝተሻል የሚያስብልሽ
የእኛማ ሙሽራ እንኳን ደስ አለሽ
እግዚአብሔር ይመስገን እኛም ደስ ብሎናል
በቤተ ክርስቲያን ሠርጋችሁ ውብ ሆኗል
እንደ ነፍስህ አድርገህ እንድትወዳት
አደራ ሰጠንህ በጌታችን ፊት
እንድታስቢለት አንቺም ለአካልሽ
አደራ ትላለች ወንጌል እናትሽ
በሥጋ ወደሙ ሕይወት አግኝታችሁ
ፍሬአችሁም ይብዛ ይባረክ ጓዳችሁ
አምላክ ያለበት ነው ይሄ ጋብቻችሁ
እስከ መጨረሻው ኑሩ ደስ ብሏችሁ

፯. ሥላሴ ይባርኳችሁ

ሥላሴ ይባርኳችሁ/፬/
በሥጋ ወደሙ ዛሬ ከበራችሁ ሥላሴ ይባርኳችሁ/፪/
እም አምላክ ትከተልህ/፬/
ፈተና እንዳይገጥምህ ድንግል ትከተልህ እም አምላክ ትከተልህ /፪/
እመ አምላክ ትከተልሽ/፬/
ፈተና እንዳይገጥምሽ ድንግል ትከተልሽ እም አምላክ ትከተልሽ /፪/
ሚካኤል በኑሯችሁ/፬/
አርምሞ ማስተዋል ትእግሥትን ይስጣችሁ ሚካኤል በኑሯችሁ/፪/
ገብርኤል ከላይ ወርዶ/፬/
እርሱ ይራዳችሁ በክንፎቹ ጋርዶ ገብርኤል ከላይ ወርዶ/፪/
ኡራኤል በምልጃው/፬/
እውቀትን ጥበብን ይስጥህ በጽዋው ኡራኤል በምልጃው/፪/
ኡራኤል በምልጃው/፬/
እውቀትን ጥበብን ይስጥሽ በጽዋው ኡራኤል በምልጃው/፪/
ጊዮርጊስ አይለያችሁ/፬/

በፈተና ጊዜ ጽናት ያሳያችሁ ጊዮርጊስ አይለያችሁ/፪/
ሥላሴ ይባርኳችሁ/፬/
በሥጋ ወደሙ ዛሬ ከበራችሁ ሥላሴ ይባርኳችሁ/፪/

፫. ሶበ ሰማዕነ ዜናከ

ሶበ ሰማዕነ ዜናከ መጻዕእነ ኀቤከ/፪/
ሶበ ሰማዕነ ዜናኪ መጻእነ ኀቤኪ/፪/
መጻእነ/፬/
እንደ ሰብአ ሰገል ነገሥተ ምሥራቅ
ዝናህን በመስማት መጣን ልንጠይቅህ
አ.ዝ... ዜናከ
እንደ ሰብአ ሰገል ነገሥተ ምሥራቅ
ዝናሽን በመስማት መጣን ልንጠይቅሽ
አ.ዝ... ዜናኪ
ብቻህን ስላየህ ሲወድህ ፈጣሪ
ፈጠረልህ ለአንተ አጽናኝ አማካሪ
አ.ዝ... ዜናከ
ብቻሽን ስላየሽ ሲወድህ ፈጣሪ
ፈጠረልሽ ለአንቺ አጽናኝ አማካሪ
አ.ዝ... ዜናኪ
የወንጌልን ትዕዛዝ በመፈጸምህ
ለዚህ ክብር በቃህ በድንግልናህ
አ.ዝ... ዜናከ
የወንጌልን ትዕዛዝ በመፈጸምሽ
ለዚህ ክብር በቃሽ በድንግልናሽ
አ.ዝ... ዜናኪ
አንቺ ቤተልሔም ቤተ ክርስቲያን
ሁለቱን አዋሐድሽ በቅዱስ ቁርባን
አ.ዝ.. ዜናከ ፣ ዜናኪ

፬. እስመ ለዓለም

እስመ ለዓለም ኧኸ/፪/
ለዓለም/፪/ እስመ ለዓለም ለዓለም በሉላቸው/፪/
ሙሽራው መልካም ኧኸ ሙሽሪት መልካም ኧኸ
ለዓለም/፪/ እስመ ለዓለም ለዓለም በሉላቸው/፪/
ደስ ይበለን በጣም ኧኸ አይግባን ፍራቻ ኧኸ
ጌታ ባርኮልናል ኧኸ ቅዱሱን ጋብቻ ኧኸ
ቃና ዘገሊላ ኧኸ ከእናቱ ጋር ገብቶ ኧኸ
ውሃውን ወደ ወይን ኧኸ ለወጠው አሳክቶ ኧኸ
ለዓለም/፪/ እስመ ለዓለም ለዓለም በሉላቸው/፪/
አዝ... እስመ ለዓለም
ዜና ጋብቻችሁ ኧኸ ለዓለም ይዳረስ ኧኸ
ይነገር ስብከቱ ኧኸ ጽፎታል ጳውሎስ ኧኸ
ዳዊትም ይጠራ ኧኸ በገና ይደርደር ኧኸ
በመዝሙር ይዘምር ኧኸ ትንቢትም ይናገር ኧኸ
ለዓለም/፪/ እስመ ለዓለም ለዓለም በሉላቸው/፪/
አዝ... እስመ ለዓለም
መድኃኔ ዓለም ይምጣ ኧኸ ይሥራ ጥበቡን ኧኸ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ መዝሙርና ሥነ ጥበባት ክፍል 2010 ዓ.ም

በግብዣችሁ ጥሯት ኧኸ ድንግል ማርያምን ኧኸ
ሐዋርያት ይምጡ ኧኸ ጻድቃንም ይጠሩ ኧኸ
ጋብቻችሁ ይመር ኧኸ መልካም ፍሬን አፍሩ ኧኸ
ለዓለም/፪/ እስመ ለዓለም ለዓለም በሉላቸው/፪/
አዝ… እስመ ለዓለም

፫. መርዓዊ ሰማያዊ

መርዓዊ ሰማያዊ/፪/
ለእመ ገብረ በዓለ በዓለ ኧኸ/፫/
ይኑሩ በሰላም/፫/ ጸንተው ዘለዓለም
ደናግል ተነሡ ያዙ መብራቱን
ሙሽራው ደረሰ አጉል እንዳንሆን
ወንጌልን ይዘዋል ጎዳናቸው ያምራል
ዓላማው መልካም ነው እነርሱን እንምሰል
የድካም ዋጋቸው/፪/
ብርሃኑን ያበራል በሃይማኖታቸው
የሙሽራው ሕይወት መልካም እንዲሆን
ካህኑ ይባርኩት ቡሩክ ሰው ይሁን
የሙሽሪት ሕይወት መልካም እንዲሆን
ካህኑ ይባርኳት ቡርክት ትሁን

፬. ግነዩ ለእግዚአብሔር

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመሔር/፪/
እስመ ለዓለም ምሕረቱ እስመ ለዓለም/፪/
እናመስግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ/፪/
በሥጋ ወደሙ ልጆችሽ አንድ ሆነዋል ዛሬ/፪/
በሥጋ ወደሙ በተክሊል የተሣሠረ/፪/
በመንግሥተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ/፪/
እመቤታችን እናታችን ማርያም/፪/
ከእነርሱ አትለይ ሁል ጊዜ ለዘለዓለም/፪/

፭. ንጽሕት ቅድስት ቡርክት

ንጽሕት ቅድስት ቡርክት
የአምላክ እናት እመቤት
ልጆችሽ ሙሽሮች ሁለቱም አንድ ሆኑ
ተዋሐዱ ተጣመሩ በቅዱስ ቁርባኑ/፪/ ኧኸ
ፍጹም መንፈሣዊ ልዩ ፍቅር
አንቺ ያለሽበት መልካም ትዳር
መሠረቱ ዛሬ ልጆችሽ
ቅድስት ሆይ ባርኪያቸው ተገኝተሽ
ድንግል ጎጇቸውን ቀድሰሽ
እውነተኛ ፍቅርን መሥርተሽ
በመካከላቸው ተገኝተሽ
ሁሉን አሰጫቸው አማልደሽ
ሙሽሮቹም አምነው በምልጃሽ
እናታችን ባርኪን ነይ ሲሉሽ
ፈጥነሽ ድረሽና በሠርጋቸው
ነይ ተመላለሺ መሐላቸው

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ መዝሙርና ሥነ ጥበባት ክፍል 2010 ዓ.ም

አንቺን ለሚወዱሽ ለሚያምኑሽ
የሕይወት አጣፋጭ አንቺ ነሽ
ሙሽሮቹም ዛሬ ይጠሩሻል
የጎጇችን ፋና ነይ ይሉሻል
ቃና ዘገሊላ ተገኝተሽ
መልካሙን ጋብቻ የባረክሽ
ዛሬም ከልጅሽ ጋር በሠርጋቸው
ነይ ተመላለሺ መሐላቸው

፳. እፁብ ድንቅ ሥራ

እፁብ ድንቅ ሥራ/፪/
በእውነት የታደለ የእግዚአብሔር ሙሽራ
በእውነት የታደለ የእግዚአብሔር ሙሽራ
ነፋሳችሁ በሰማይ ርግብ ትመስላለች
ከመላእክት ጋራ ዛሬ ዘምራለች/፪/
እልል እልል በሉ ክርስቲያኖች ሁሉ
ያበራ ጀመረ ሙሽራው ጸዳሉ
ያበራ ጀመረ ሙሽሪት ጸዳሏ
ከክርስቶስ ሰላም እንዴት ይርቃል ሰው
ሥጋና ደሙን ሳይሳሳ ከሰጠው/፪/
የመንፈስ ቅዱስ ሕፃናት በመሆን
በሥጋ ወደሙ መቀደስ አለብን/፪/
በእግዚአብሔር ተባርኮ የመኖር ምሥጢር
የዘለዓለም ሕይወት ያሰጣል ፍቅር/፪/
ሥጋውን ፍሪዳ ደሙን መጠጥ አድርጎ
ሰጥቶናል አማኑኤል ሕይወቱን ሰወቶ/፪/

፪. የቃና ደስታ

የቃና ደስታ ዛሬ ተደገመ
ጌታ ከእናቱ ጋር በሠርጉ ታደመ
የዘለዓለም አምላክ ስላለ በዚህ ቤት
ሙሽራው ሙሽሪት አገኙ በረከት
መርዓት ተሸልማ የድንግልና አክሊል
እዩት ሥርዓቱ እጅግ ያስደስታል
አንድ አካል ሙሽሮች እዩአቸው ሲያበሩ
በወንጌሉ በተክሊሉ ሄዱ እየተመሩ
እንግዳቸው ብዙ ድንኳናቸው ሙሉ
ጌታ ከእናቱ ጋር አለ በመሀሉ
የወይን ጋኖቹ ዛሬ ሙሉ ናቸው
አማኑኤል ድንግል ማርያም ስላሉ ቤታቸው
በክብር ታጅቦ ሲመጣ መርዓዊ
እጅግ ያስደስታል አይደለም ምድራዊ
ዛሬ በዚህ ድንኳን ተድላ ተደረገ
በአማኑኤል በአምላካቸው ስለተባረከ
በተክሊል በቁርባኑ የሆነ አንድነት
አይነጣጠልም ዳግም ወደ ሁለት
ሙሽሪት ሙሽራው ተደሰቱ ዛሬ
በሠርጋቸው ተገለጸ የእምነታቸው ፍሬ

፲. እሠይ እሠይ

እሠይ እሠይ እሠይ/፪/
የተዋሕዶ ምሥጢር ስናይ
እሠይ እሠይ በአዳም ተጀምሮ
“ “ የአንድ አካል ምሥጢር
“ “ በገነት ሲኖሩ
“ “ በጽድቅ ምድር
አካሌ ናት አላት ሔዋንን በፍቅር
እሠይ እሠይ መካን ሆነው ሳሉ
“ “ ሐና እና ኢያቄም
“ “ የጸናው አንድነት
“ “ አልተነጣጠለም
“ “ በእምነት ቢቆሙ
“ “ በጾም በጸሎት
ድንግል ተወለደች ልትሆን መድኃኒት
እሠይ እሠይ ዛሬ በሙሽሮች
“ “ ይህንን አይተናል
“ “ በቅዱስ ጋብቻ
“ “ በማይነጣጠል
ምሥጢር ተፈጸመ በሥርዓት ተክሊል
እሠይ እሠይ የተዋሕዶ ምሥጢር
“ “ እጅግ የጠለቀ
“ “ በአመኑት ልቡና
“ “ ፈጽሞ ታወቀ
ዛሬ በሙሽሮች ክብር ተደነቀ

፲፩. እንደ እብርሃም

እንደ አብርሃም እንደ ሣራ/፪/
ሥላሴ ይኑሩ ከእናንተ ጋራ/፪/
ቤታችሁ ይባረክ በረከት ይሙላ
ፈቅደው ይስጧችሁ ሰላምና ተድላ
ቤቱም የሥላሴ ይሁንላችሁ
ዘወትር ይኑሩ መሐከላችሁ
ጌታዬ በይው ውድሽ ነውና
እህቴ በላት ሥጋህ ናትና
ጽድቅ የተመላ ፍሬ ይስጡአችሁ
አብርሃም ሣራን ሁኑ ጸንታችሁ
ቤታችሁ ይከፈት ለእንግዳ ሰው
ከፍላችሁ ስጡ ለተራበው
መልካሙን ፍሬ አፍሩ ተግታችሁ
ስመ ሥላሴን እያሰባችሁ
ጌታዬ በይው ውድሽ ነውና
እህቴ በላት ሥጋህ ናትና
ጽድቅ የተመላ ፍሬ ይስጣችሁ
አብርሃም ሣራን ሁኑ ጸንታችሁ

፲፪. ሙሽራው ደስ ይበልህ

ሙሽራው ደስ ይበልህ/፪/

ፈቃዱ ሆኖ ጌታህ ፍጽም በረከት ሰጠህ
ሙሽሪት ደስ ይበልሽ/፪/
ፈቃዱ ሆኖ ጌታሽ ፍጹም በረከት ሰጠሽ
ሁለት አይደለም ቃላቸው
ዘወትር አንድ ነው ድምጻቸው
የኑሮን ሕይወት እንዲገፉ
በአንድነት ሆነው ተሰለፉ
ሁለት አይደለም ኑሮአቸው
ከእንግዲህ አንድ ነው ጎጆአቸው
መሠረት ጣሪያ ግድግዳው
እግዚአብሔር ነው ምሰሶው
ምድራዊ አይደለም ሰማያዊ
የማይመረመር ምሥጢራዊ
በሥጋ ወደሙ እንደ ሆነው
ሙሽሪትና ሙሽራው

፲፮. ደመቀ አበራልን

ደመቀ አበራልን የአማኑኤል ሥራ/፪/
ሙሽሮቹ ሆኑ አብርሃም ወሣራ
በቤተ ክርስቲያን ጥላ ተጠልለው
ተክሊል አድርገዋል ሙሽሪት ሙሽራው
ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ስለተሰጣቸው
ሙሽሪት ሙሽራው አበራ ገጻቸው
የተራራቀ አካል አንድ ሆነ በተክሊል
እግዚአብሔር ይመስገን እልል/፪ / እንበል
አጥንትሽ ከአጥንቱ ሥጋሽ ከሥጋዬ
አዳም የሰበከው ይኸው ዛሬ ታየ
የተክሊል ብርሃኗ በእኛ መሐል በርቶ
ረቂቅ አንድነት ታየ በእርሷ ጎልቶ
ይህን ድንቅ ነገር ለማየት ያበቃን
ምስጢሩን የሚገልጥ እግዚአብሔር ይመስገን
ነጭ መጎናጸፊያን በአንድ ተጎናጽፈው
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እራሱ በጥላው
ሙሽሪት ሙሽራው በፍቅር ተሸነፉ
ለቁርባን መቁረቢያ ነጭ ልብስ እሰፉ

፲፯. ሙሽሮች እንኳን ደስ አላችሁ

ሙሽሮች እንኳን ደስ አላችሁ/፪/
ለዚህ ቀን ይኸው ደረሳችሁ
በአምላክ ፊት እጅግ ከበራችሁ
በእግዚአብሔር ቸርነት በመልካም ፈቃዱ
በቅዱስ ቁርባኑ ዛሬ ተዋሐዱ/፪/
በሥርዓተ ተክሊል በሥጋ ወደሙ
በመድኃኔዓለም ፊት ጋብቻ ፈጸሙ/፪/
በቤተ ክርስቲያን በፈጣሪያቸው ፊት
ሁለቱም አንድ ሆኑ በዚህች ቅድስት እለት/፪/
አንድ የሚያደርጋቸው ተነበ ወንጌሉ
በካህኑ መስቀል በረከት ታደሉ/፪/

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ መዝሙርና ሥነ ጥበባት ክፍል 2010 ዓ.ም

በወንጌል ትዕዛዝ በሐዋርያት ቃል
በእመ ብርሃን ፊት ጋብቻቸው ጸድቋል/፪/
በአምላክ ሥጋና ደም ሁለቱም ታተሙ
የኅብረት ቃል ኪዳን ባንድ ላይ አሰሙ/፪/
አጽንቶ የሚያጸድቅ የማይለያያቸው
ክቡር ቃል ስላለ በመካከላቸው/፪/
እስከ መጨረሻው አንድ አካል ሆነዋል
የአምላክ ሥጋና ደም አስተሳስሯቸዋል/፪/

፲፱. አጅቡት በእልልታ

አጅቡት በእልልታ ሲወጣ ሙሽራው
ፍጹም የሚያስደስት የሠርጉ እለት ነው
ዘመዶቹ ሁሉ ተቀበሉት ውጡ
የሙሽራው መምጫ አሁን ነው ሰዓቱ
እልል እልል እንበል እንዘምር በደስታ
ይህን ላደረገ ለሠራዊት ጌታ
ሁሉንም በጊዜው ይፈጽማልና
ይኸው አበቃቸው ለዚህ መልካም ዜና
ሙሽሪት ተደሰች ዝምታው ምንድነው
የዳግም ልደትሽ የሠርግሽ እለት ነው
አዳም ጎንሽ ሆኖ ሔዋን ሆይ ሲልሽ
መንፈሳዊ ሐሴት ይሙላ በልብሽ
እህት ወንድሞቿ እናት እና አባቷ
ተነሡ ዘምሩ ለልጃችሁ ደስታ

መግቢያዋ ነውና ወደ ቤቷ ዛሬ
ወደ አዲስ ጎጆዋ ሽኟት በዝማሬ
ቤተሰቦችሽን ሁሉንም ትተሽ
መሄድሽ ነውና ወደ መኖሪያሽ
ከአማኑኤል ጋራ ባልሽን ይዘሽ
ተነሽ ሙሽራዬ ደርሷል ሰዓትሽ
ከድንግልም ጋራ ሚስትህን ይዘህ
ተነሥ ወንድሜ ሆይ ደርሷል ሰዓትህ

፳. በሠርጋችን እለት

በሠርጋችን እለት እንድትባርከን
ጌታ ጠርተንሃል በእምነት ሆነን
ከእናትህ ጋራ ከእመቤታችን
ከመላእክት ጋር ና በሠርጋችን
ከሐዋርያት ጋር ና በሠርጋችን
ከወዳጆችህ ጋር ና በሠርጋችን
በገሊላ መንደር እንደተገኘህ
ና በእኛ ድንኳንም ጌታ ስንጠራህ
ስለ እናትህ ብለህ ጌታችን እንዳትቀር
አንተ ነህ ክብራችን የቤታችን ፍቅር
በጎደለው ሁሉ እየጨመርሽልን
ቤታችንን ሁሉ ሙይው እናታችን
ለአገልጋዮቹም ድንግል ንገሪያቸው
ጠርተን እንዳናፍር ጋኖቹን ይሙላቸው

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ መዝሙርና ሥነ ጥበባት

ነይ ከልጅሽ ጋራ እመቤታችን
እንድታሚይልን የጎደለውን
ንገሪው ለልጅሽ ባዶው እንዲሞላ
በረከት የርሱ ነው ቤታችንን ይሙላ

፳፩. የምሥራች

የምሥራች ደስ ይበላችሁ/፪/
አሸብርቆ ዋለ ሙሽሮች ሠርጋችሁ/፪/
ሕይወታችሁ ሰላማዊ ፍጹም ፍቅር/፪/
እንደ ጽጌረዳ እንደ ዓደይ ፈክቶ የሚኖር
አማኑኤል ያርገው መልካም ትስስር
መተሳሰብ መከባበር ይሁን ግብራችሁ/፪/
ሠርጎ እንዳይገባ ዲያብሎስ በትዳራችሁ
በጾም ጸሎት ይታጠር ሙሽሮች ጎጇችሁ
እግሮቻችሁ ይገሥግሱ ወደ እውነት/፪/
አማናዊው ማዕድ ክርስቶስ ወዳለበት
በልባችሁ አኑሩት ታላቁን አባት
አይኖቻችሁ የጎረቤት አይመልከቱ/፪/
ለወሬ ለሐሜት ጆሮአችሁ አይከፈቱ
በችግር በደስታ በጾም ጸሎት በርቱ
ድንግል ማርያም ቅድስት እናት ለምኝላቸው/፪/
የሚፈልጉትን ከልጅሽ አንቺ አሰጫቸው
በሰማይ በምድር ምልጃሽ አይራቃቸው

፳፪. ሁለቱም አንድ ሆኑ

ሁለቱም አንድ ሆኑ ዛሬ/፪/ ኧኸ/፪/
በእግዚአብሔር በሕያው ቃሉ
ሁለቱም አንድ ሆኑ ዛሬ
ወንድና ሴት አርጎ የፈጠራቸው
በኋላም በቃሉ አንድ ያረጋቸው
እናትና አባቱን የአዳም ልጅ ይተዋል
ከሚስቱም ጋር በሰላም በአንድ ይተባበራል
ሁለቱም አንድ ሥጋ አብረው ይኖራሉ
ብሎ አስተምሮናል ጌታችን በቃሉ
አንድ ሥጋ ናቸው አይደሉም ሁለት
የባልና የሚስት ሕይወት ወደፊት
እንግዲህ እግዚአብሔር ካጣመራችሁ
በሆነው ባልሆነው ሰው አይለያችሁ
ለወገኖቻችሁ ምሳሌ ሆናችሁ
በክርስትና ፍቅር በአንድ ያቁማችሁ
ምንጣፋችሁ ብሩሕ መኝታችሁ ንጹሕ
ስለሆነላችሁ እንኳን ደስ አላችሁ
ዓለም እንዲደነቅ ጠላት እንዲያፍር
በኀዘን በደስታ ይኑራችሁ ፍቅር

፳፫.ተፈሥሒ ቤተ ክርስቲያን

ተፈሥሒ ቤተ ክርስቲያን ተፈሥሒ ቤተ ሥላሴ
ያሳደግሻቸው ልጆችሽ አብርሃም ሳራ ሲሆኑልሽ/፪/

ትምሕርትሽ ገብቷቸው የወንጌሉ ቃል
በኑሮ ሊያበሩ ይኸው መጥተዋል
በክርሥቶስ ፈቃድ በቃሉ ተመርተው
ለአለም መሰከሩ ተራራ ላይ ቆመው ....ተፈሥሒ
ከእቅቡ በታች አይደለም መብራቱ
በራ እንጅ ለሁሉ ከእነ በረከቱ
ጢስ የሌለው ሻማ ደምቀው የከበሩ
ልጆችሽ ሙሽሮች እንደ ጧፍ አበሩ .....ተፈሥሒ
ሰላም ላንች ይሁን ደስ ይበልሽ በጣም
የዘራሽው ማሳ ፍሬውን ሲሸከም
ካባ ደረብሽለት/ላት ለውዱ/ዷ ሙሽራ
አክሊል ደፋሽለት/ላት ከምርቃት ጋራ......ተፈሥሒ
ቃልሽ ይለውጣል ግሩም ነው ኃያል
መንዝራዎቹን ድንግል ያደርጋል
ተገለጠ ክብርሽ ለሙሽሮች ዛሬ
መከር ሆኖልሻለል ባፈራሽው ፍሬ ......ተፈሥሒ

፳፬. ሙሽሮች እንኳን ደስ አላችሁ

ሙሽሮች እንኳን ደስ አላችሁ /2/
ለዚህ ቀን ይኸው ደረሳችሁ
በአምላክ ፊት እጅግ ከበራችሁ
በእግዚአብሔር ቸረነት በመልካም ፈቃዱ
በቅደስ ቁርባኑ ዛሬ ተዋሐዱ /2/
በሥርዓት ተክሊል በሥጋ ወደሙ
በመድኃኔዓለም ፊት ጋብቻን ፈፀሙ /2/
በቤተ ክርስቲያን በፈጣሪያቸው ፊት
ሁለቱም አንድ ሆኑ በዚህች ቅድስት እለት /2/
አንድ የሚያደርጋቸው ተነቦ ወንጌሉ
በካህኑ መስቀሉ በረከት ታደሉ /2/
በወንጌሌ ትዕዛዝ በሐዋርያት ቃል
በእመብርሃን ፊት ጋብቻቸው ፀድቋል /2/
በአምላክ ስጋና ደም ሁለቱም ታተሙ
ህብረት ቃሌ ኪዳን በአንዴ ሊይ አሰሙ /2/
አፅንቶ የሚያፀድቅ የማይለያያቸው
ክቡር ቃል ስላለ በመካከላቸው /2/
እስከመጨረሻው አንድ አካል ሆነዋል
የአማኑኤል ስጋ አስተምሯቸዋል/2/

፳፭. ድንግልን ጥሩ

የዶኪማስን እመቤት ጥሩ
ወይን ጠጅ አልቆ ሳትማረሩ
እንድትረዳችሁ ድንግልን ጥሩ
ባድ እንዳይሆኑ ጋኖቻችሁ
የምታቀርቡት አልቆባችሁ
ጭንቀት ሳይገባ በኑሮአችሁ
የመቀረዝ መብራት ስለሆናችሁ
የነፍስ ትግል ቢበዛባችሁ
ሳትወድቁ ድንገት ተሸንፋችሁ
ሃይለኛ ቢሆን የጠላት መረብ
ስለማይተኛ ህሜት ከማቅረብ
የውርደት ሸማ ለማከናነብ
ሳያማክሯት የምታውቀውን
ማለቁን አይታ የጎደለውን

እንድትሰጠን የሚጠቅመንን

፳፯. ተነስ ሙሽራዬ

ተነስ ሙሽራዬ አለብህ እንግዳ
እንደ ዶኪማስ ቤት ቤትህን አሰናዳ
ቸር አምላካችን ነው የዚህ ቤት እንግዳ
እመቤታችን ናት የዚህ ቤት እንግዳ
 አምላክ አያዳላም ሁሉንም ይሰማል
 ጥሪህን አክብሮ በቤትህ ይገባል
 ምንም አትጨነቅ ሰላም ይሁንልህ
 በእምነት አስተናግደው ይሙላና ሃሳብህ /2/
የዓለም ፈጣሪ ጌታችን በቤትህ
ከእናቱ ጋራ መገኘቱን አይተህ
በልብህ አኑረው ታላቅ ቸርነቱን
የፍቅሩን በረከት ድንቅ ታምራቱን/2/
 በቤትህ የገባ አንተ የጠራኸው
 አልፋና ኦሜጋ ሁለን አድራጊ ነው
 ታምራት ያደርጋል በእጆቹ ሥራ
 መድኅን ክርስቶስ ከእናቱ ጋራ/2/

፳፯. አዳም ሆይ

አዳም ሆይ እህት አገኘህ /2/
በሃሴት ይሙላ ልቡናህ ደስ ይበልህ
ሔዋን ሆይ ወንድም አገኘሽ /2/
በሃሴት ይሙላ ልቡናሽ ደስ ይበልሽ
 ብቻህን መሆንህን እግዚአብሔር አይቶ
 የከበደ እንቅልፍን በአንተ ላይ አምጥቶ
 አጥንት ወሰደና አንዷን ከጎንህ
 እህት እንድትሆንህ ሔዋንን ሰጠህ
ከጎኑ ተፈጥረሽ በሥላሴ ጥበብ
አክብረው ባልሽን ተዋደዱ ከልብ
አዳም ከጎንሽ ነው የሚያስብልሽ
የአምላክን ስጦታ ውሰጅው ፈቅደሽ
 አካልህ ሔዋን ናት ያንተ እጣ ፈንታ
 አምላክ ባረካችሁ በብዙ ደስታ
 የኑሮን ተካፋይ አምላክ ከሰጠህ
 ሕይወቴ ነሽ ብለህ ሂድ ወደ ሚስትህ

፳፰. ቃና ዘገሊላ

ቃና ዘገሊላ /2/ በዚያ በሠርግ ቤት
ተገኝተሻል ድንግል ከልጅሽ ጋራ
ተገኝተሃል ጌታ ከእናትህ ጋራ
 እድምተኞች ሞልተው የተጋበዙት
 ሲበለ ሲጠጡ ወይኑ አልቆበት
 ድንግል እናታችን ቤዛዊት ዓለም
 አንች ደረስሽለት ሆንሽው አማላጅ
አንተ እያለህስ ማፈር የለባቸው
ሁሉ ይቻልሃል ወይኑን ሙላላቸው
ማድጋው ባዶ ነው ብለሽ የተናገርሽ
ጌታን ያሳሰብሽው እመቤታችን ነሽ
 የጌታ አምላክነት የተገለጠበት
 ምንኛ ታደለ የእነ ዶኪማስ ቤት
 ዛሬም ይሄው በዚህ በሠርገኞቹ ቤት
 በረከት ፈሰሰ በአምላክ ቸርነት
ውኃው ተለውጦ የወይን ጠጅ ሲሆን

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ መዝሙርና ሥነ ጥበባት ክፍል 2010 ዓ.ም

በቃና ገሊላ ሁላችን አየን
እግዚአብሔር ከኖረ በመካከላችን
ሁሌም ይሰጠናል ይህን መሰል ወይን

፳፱ ድንቅ ነው በጣም

ድንቅ ነው በጣም ድንቅ ነው ፪
በሠርጋችሁ እለት ተገኘ መድኃኔዓለም
በሥርጋችሁ እለት ተገኘች ድንግል ማርያም
በቃልህ ተመርተው ለዚህ ቀን በቅተዋል
በፊትህ ጋብቻን ይኸው ፈጽመዋል
በፈሰሰው ደምህ ሁብረት መሥርተዋል
በሥጋም በነፍስም /2/ ያንተ ነን ብለዋል
ከአዳም አንድ አጥንት ከጎኑ ወስደህ
አጋር እንድትሆነው ሔዋንን ሰጠህ
ሁለቱንም ባርከህ እንደፈጠርሀቸው
ዛሬም ለሙሽሮች/2/ ሰላምን ስጣቸው
ጌታ ሆይ በህግህ በቃልህ መሠረት
አንድ ሁነዋልና በዚች ቅድስት ዕለት
እርሱንም እርሷንም ባርከህ ቀድሳቸው
ዘላለማዊ ፍቅር /2/ ጽናትን ስጣቸው
የዲያብሎስ ተንኮል እንዳያስታቸው
እስከመጨረሻው ጋሻ ሁንላቸው
ከቅድስቲቷ ቤት ሁለቱም ሳይርቁ
ጽናቱን ስጣቸው/2/ አብረው እንዲዘልቁ

፴፩.ኑ ተመልከቱልገኝ

ኑ ተመልከቱልኝ የአማኑኤልን ሥራ
ኑ ተመልከቱልኝ የእመቤቴን ሥራ
ሙሽሮቹ ሆኑ አብርሃም ወሣራ/2/
ሐናና ኢያቄም በጸሎት ሲተጉ
በፈጣሪያቸው ፊት መልካሙን ቢያደርጉ
በቅዱስ ጋብቻ ጸንተው ቢራመዱ
የአምላክን እናት ድንግልን ወለዱ /2/
ቀን ከሌት ሲጸልይ ዘካርስ ካህን
ኤልሳቤጥም ተግታ ፈጣሪን ብትለምን
በእግዚአብሔር ጥበብ በስተርጅናቸው
ቅዱስ ዮሐንስን አክብሮ ሰጣቸው/2/
ጸጋ ዘአብና ቅድስት እግዚእ ኀሪያ
ለመልካም ጋብቻ ሆነዋል አርዓያ
ተክለሃይማኖትን ጻድቁን ያፈሩት
ቀን ከሌት ተግተው ነው በጾምና ጸሎት/2/

፴፪.በምድራዊ ሕይወት

በምድራዊ ሕይወት በፈተና ቦታ
ማርያም ትጠብቅህ/ሽ እጆቿን ዘርግታ
ድንግል ትጠብቅህ/ሽ እጆቿን ዘርግታ

፴፫. ትዌድሶ

ትዌድሶ መርዓት ወትብሎ/፪/
ወልድ እኁየ ቃልከ አዳም/፬/ ኧኸ

፴፬. መጽአ ዘመጽአ

መጽአ ዘመጽአ እምላእሉ/፪/
መርዓዊ መጽአ/፪/ ተቀበሉ ፃኡ ተቀበሉ/፪/

፻፷፭. መጽአ መርዓዊ

መጽአ መርዓዊ ፍስሐ ለኵሉ/፪/
በሰላም ፃኡ ተቀበሉ/፬/ ኧኸ

፻፷፮. በቃና ዘገሊላ

በቃና ዘገሊላ/፪/
ዘገሊላ ከብካብ ኮነ/፬/ ኧኸ

፻፷፯. ካህናት ተንሥኡ

ካህናት ተንሥኡ/፪/ ለተናብቦ/፪/
እንዘ ይብሉ ንሴብሖ/፪/ እንዘ ይብሉ ንሴብሖ/፪/

፻፷፰. ተቀደሲ

ተቀደሲ ወንስኢ ኃይለ ኦ________ /፪/
እስመ ናሁ ንጉሥኪ መጽአ ______ /፪/

፻፷፱. ተአምረ ወመንከረ

ተአምረ ወመንከረ ገብረ መድኃኒነ/፪/
በቃና ዘገሊላ/፪/ ከብካብ ኮነ/፪/

፻፸. ትብሎ መርዓት

ትብሎ መርዓት/፪/ ለመርዓዊሃ/፪/
ኧኸ እስከ አመ ፈቀደ/፪/ አፈቅሮ/፪/

፻፸፩. አማህኩኪ

አማኅኩኪ ቅድስት ቤተክርስቲያን
ከብካብ ኮነ በቃና ዘገሊላ/፪/
ደምጸ እንዚራ ውስተ ቤተ________/፪/

፻፸፪. ጥኢሞ አንከረ

ጥኢሞ አንከረ ሊቀ ምርፋቅ/፪/
በረከተ/፫/ ዘአምላክ ገብረ/፪/ ኧኸ

፻፸፫. የማኑ ተኃቅፈኒ

የማኑ ተኃቅፈኒ ወጸጋሙ ታህተ ርእስየ/፪/
ትብሎ መርዓት ትብሎ/፬/ መርዓት ለመርዓዊሃ/፪

፻፸፬.ባርክ ዘንተ ከብካበ

ባርክ ዘንተ ከብካበ/፬/
ንጉሠ ስብሓት/፪/ ባርክ ዘንተ ከብካብ/፪/

፻፸፭. ብጹእ አንተ

ብጹእ አንተ/፮/
ወብእሲትከ ከመወይን ሥሙር/፬/

፻፸፮. አርኅዉ

አርኅዉ ኆኃተ ለንጉሠ ስብሓት ዘይቤ/፪/
ተሰምዐ ቃለ ቀርን ወደምጸ ይባቤ/፪/

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ መዝሙርና ሥነ ጥበባት ክፍል 2010 ዓ.ም

፺፯. ወቡሩክ ዘርከ

__________ እጉነ ወቡሩክ ዘርከ/፪/
ተፈስሐ/፫/ ምእመናን ይብሉከ/፪/
__________እኅትነ ወቡሩክ ዘርኪ/፪/
ተፈስሒ/፫/ ምእመናን ይብሉኪ/፪/

፺፰. መርዓዊ ሕግከ

መርዓዊ ሕግከ/፪/ አርሞንኤም/፪/
ሶበ መጽአ ቃል እንበለ ድካም
እም ደመና/፫/ ልብስከ ግሩም
እም ደመና ልብስከ ግሩም

፺፱. ከብካብ ኮነ

ከብካብ ኮነ/፮/ ኸኸ
ውስተ ቤተ________ /፬/

፻. መርዓዊ ስቡሕ

መርዓዊ ስቡሕ/፪/ ንጉሥ ውእቱ
ወእስከ ለዓለም/፪/ ንጉሥ ውእቱ ኸኸ

፻፩. መርዓዊ ሠናይ

መርዓዊ ሠናይ ሠናይ/፪/
ወመርዓቱ ትመስል ፀሐይ/፪/ ኸኸ

፻፪. ዘእግዚአብሔር አስተጻመረ

ዘእግዚአብሔር አስተጻመረ ኢይፍልጥ ሰብእ
ብእሲ ወብእሲት አሐዱ አካል/፪/

፻፫. ወይቤላ

ወይቤላ ውእቱ መርዓዊ ሰላም ለኪ/፪/
ሰላም ዚአየ የሀሉ ምስሌኪ/፪/

፻፬. ሕገ ሰብእናሁ

ሕገ ሰብእናሁ አቀበ/፪/ በተደንግሎ/፪/
ወፈጸመ/፭/ በወንጌል ዘሀሎ/፪/

፻፭. እንዘ ስውር

እንዘ ስውር እምኔነ ይእዜሰ ክሡተ ኮነ/፪/
ተአምረ ወመንክረ ገብረ መድኃኒነ
በቃና ዘገሊላ ከብካብ ኮነ ማየ ረሰየ ወይነ /፪/

፻፮. ደስ አለው ጌታ

ደስ አለው ጌታ በሙሽሮችደስ አለው ጌታኸኸ /፪/
በቅዱስ ቁርባን ተወስነው ደስ አለው ጌታ /፪/
ደስ አላት ድንግል በሙሽሮች ደስ አላት ድንግል ኸኸ /፪/
በቅዱስ ቁርባን ተወስነው ደስ አላት ድንግል /፪/

፻፯. ደስ አላት

ደስ አላት ቤተክርስቲያን በጣም ደስ አላት/፪/
ሙሽሪት ሙሽራው ልጆቿ/፪/

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ መዝሙርና ሥነ ጥበባት

በተክሊል በቁርባን ተዋሐዱላት /፪/

፶፰. ትብሎ መርዓት

ትብሎ መርዓት ሠናይ አንተ ለመርዓዊሃ _______ /፪/

ይጥእመኒ ቃልከ/፪/ እም አስካለ ወይን/፪/

፶፱ በምድራዊ ሕይወት

በምድራዊ ሕይወት (2)በፈተና ቦታ

ማርያም ትጠብቅህ/ሽ እጆቿን ዘርግታ} ፬

ድንግል ትጠብቅህ/ሽ እጆቿን ዘርግታ}

፷ እያቄም ወሐና

እያቄም ወሐና (፬)

ሙሽሮቹ ያብባሉ ገና ኧኸ

፷፩ ንሴብሖ ለአምላከ እዝራ

ንሴብሖ /፬/ለአምላከ እዝራ

እርሱን ለፈጠረ እርሷንም ለሰራ /፬/

ንሴብሖ ለአምላከ እዝራ}

፷፪. አንቲ ውእቱ

አንቲ ውእቱ መንፈሳዊት .... አንቲ ውእቱ.

ዘኀረዩኪ ....2 _ኧኸ

፷፫. ተሰምዐ

ተሰምዐ በዛቲ ዓለም /4/

በዛቲ ዓለም/2/ ተሰምዐ በዛቲ ዓለም/2/

፷፬. እልል እልል

እልል እልል ደስ ይበለን እልል ደስ ይበለን/2/

አጅበን መጣን ሙሽሮችን እልል ብላችሁ ተቀበሉን /4/

፷፭. መርዓትከ

መርዓትከ/3/

ለህያ ሰናይ /2/ መርዓትከ

፷፮. ንሴብሖ

ንሴብሖ/2/ ለአምላከ ዕዝራ

እርሱን ለፈጠረ እርሷንም ለሰራ

ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ/2/

፷፯. በከመ ይቤ

በከመ ይቤ ዳዊት በመዝሙር /2/

አንተ መርዓዊ ለዓለም

አንተ መርዓዊ ለዓለም

፷፰. በረከት የሰጠ

በረከት የሰጠ ለአብርሃም ለሣራ

ባረከልን /2/ እኒህን ሙሽራ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ መዝሙርና ሥነ ጥበባት ክፍል 2010 ዓ.ም

፺፱. ዘበሰማያት

ዘበሰማያት አቡነ ዘበሰማያት
ከዚህ ቤት /5/ ይሙላ በርከት

፻. አንከርወ ለማይ

አንከርወ ለማይ አእኩትዎ ለኢየሱስ /2/
በእንተ ማይ ዘኮነ ወይነ በእንተ ማይ ዘኮነ **/2/**

፻፩.በከመ ሰምዕነ

በከመ ሰማዕነ ከማሁ ርኢነ /2/
ወይነ ቃና /፫/ በቤትከ/ኪ/ ኮነ /2/

፻፪.ጥቀ ሰነይኪ

ጥቀ ሰነይከ ወጥቀ አደምኪ /2/
ሥሙረ በቀልት/3/ ይመስል ቆምኪ ጥቀ ሰነይኪ/2/16

፻፫ ርስኢ ሕዝበኪ

ርስኢ ሕዝበኪ ወቤተ አቡኪ/2/
እስመ ፈተወ መርዓዊ ሥነኪ /2/

፻፬. ሰሎሞን ይቤላ

ሰሎሞን ይቤላ ሰሎሞን ይቤላ
አዕይንትኪ ዘርግብ ሰሎሞን ይቤላ /2/

፻፭.ወይቤላ እኅትየ

ወይቤላ እኅትየ /2/
እኅትየ ....አፅምኪ እም አፅምየ ይኩን /2/ ኽሽ

፻፮. ከመ ይንስኡ

ከመ ይንስኡ <u>ዐስበ እሴቶሙ</u>/2/
አክሊል ንፁህ ዲበ ርእሶሙ /2/ኽሽ

፻፯. እምግርማሁ

እምግርማሁ ትርእድ ምድር መርዓዊ ስቡሕ ዘለዓለም /2/
ወእስከ ለዓለም /2/ ካህን (ስቡሕ) ዉእቱ/2/ ኽሽ

፻፰. ማየ ወይነ ረሰየ

ማየ ወይነ ረሰየ /2/
መዓዛ ቃልከ ይትወከፍ ጸሎትየ /2/ኽሽ

፻፱. በደህና

———በደህና———በሠላም
ክልኤቱ ይንበሩዘለዓለም
———በደህና———በሠላም
ሁለቱም ይኑሩ ዘለዓለም

፻፲.ቤተ ቃና

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ መዝሙርና ሥነ ጥበባት ክፍል 2010 ዓ.ም

ወረደ መንፈስ ቅዱስ /2/

ቤተ ቃና ዘወይን /2/ዘወይን /2/ቤተ ቃና ዘወይን

፳፩. ጸዉ ተቀበሉ

ጸዉ ተቀበሉ /6/

መርዓዊ መጽዓ /2/ ተቀበሉ ጸዉ ተቀበሉ

፳፪. ሙሽራው ደስ አለው

ሙሽራው ደስ አለው በስርዓተ ተክሊል/ቁርባን/ ሲያገባ ኧሽ

አሸበረቀ ደመቀ አጌጠ በወንጌል አበባ

ሙሽሪት ደስ አላት በስርዓተ ተክሊል /ቁርባን/ ስታገባ ኧሽ

አሸበረቀች ደመቀች አጌጠች በወንጌል አበባ

፳፫.የሀብከ ዮም

የሀብከ ዮም የሀብከ መድኃኔዓለም /2/

እድሜ ማቱሳላ ወአብርሃም /2/

፳፬.ብእሴ ወብእሲት

ብእሲ ወብእሲት /4/

አሐዱ አካል ኮኑ /4/ አሐዱ አካል

፳፭.ያስደስታል

ያስደስታል /3/ የእኛ እምነታችን

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የጋብቻ ስርዓታችን

ተፈጸመ /3/ ዛሬ ሰርጋችሁው

ምስጋና ይግባው እንላለን /2/ ቸሩ አምላካችን

፳፮.በትፍስሕት

በትፍስሕት ወበሐሴት

ተቀበልዋ ለመርዓት /4/